# አንድነት ለፍትህ የሻማ ማብራት በኮለን ከተማ፡ ጀርመን ተካሄደ

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ግፈኛና ዘረኛ ቡድን  ስር ሌላ ወንጀል ሳይኖርባቸው በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ብቻ ወደ እስር ቤት መጣላቸውንና በዴሞክራሲያ ስም ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶችን በሰላም ስም መደብደብ፡ እንግልት፡ መታሰርና መገደል የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን እድል ሆኖ የቀጠለበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡

የወያኔ ግፈኛና ዘረኛ መንግስት ስልጣን ላይ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ ፍትህ በኢትዮጵያ ውስጥ ፍጹም እንደሌለና በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሲገደሉ፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ በእስር ቤቶች ታጉረዋል፡፡ እንደ ምሳሌ ወያኔ ስልጣን ከወጣበት ከግንቦት 1983 ጀምሮ የኢሕአፓ መሪዎችን በጉርጓድ እስርቤቶች አስሮ ዬት እንዳሉ የማይታወቅበት፤ በቀይ መስቀል ተወካዮች እንኳ እንዳይጎበኙ መደረጋቸው፡ አቶ አበራ የማነ አብ ለእርቅና ሰላም አዲስ አበባ ሄደው እንዲታሰሩ ተደርገው የወያኔ ፍርድ ቤት ከለቀቃቸው በኋላ ግፈኛው የወያኔ ባለስልጣናት ፍላጎት መሰረት ከእስር ቤት እንዳይወጡ መደረጋቸውና 25 ዓመት ተፈረደባቸው  ተብሎ ሰምተናል፡፡የወያኔ ባለስልጣናት የራሱን የወያኔን ህግ በመጣስ ከራሳቸው ህግ በላይ ያሳዩበት ሁኔታ ተከስቷል፡፡አቶ ስዬ አብርሃም ሌላ ወንጀል በመስራታቸው ሳይሆን ከወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር የተለየ አስተሳሰብ ስላላቸው ብቻ ወደ እስር ቤት ተወርውረዋል፡፡ከግንቦት 1997 ዓ.ም. ምርጫ ከፍተኛውን ድምጽ በማግኘት ምርጫውን በማሸነፋቸው የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር የሰጠው መልስ ማንቋሸሽ፡ እንግልት፡ ዱላና ግድያ ነበር፡፡ከዚህ በኋላ የቅንጅት መሪዎችን፡ የህብረት አባላትን፡ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን" ጋዜጠኞችን፡ መምህራንን፡ ሰራተኛውን፡ ገበሬውን፡ በአጠቃላይ በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት በእስር ቤቶች ታጉረው እየተሰቃዩ የሚገኙበት ወቅት ነው፡፡ከዚሁ ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ በኋላ  ባደረገው ጭፍጨፋ በራሱ አጣሪ ኮሚሽን ሪፖርት መሰረት 193 በግፈኛው በወያኔ አግአዚና ፌደራል ፓሊስ መገደላቸውን ተረጋግጧል፡፡

በኮለን ከተማ ጀርመን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ወቅት በእስር ቤቶች የሚገኙት የፖለቲካ እሰረኞች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታዎች እንዲፈቱ ለመማጸንና የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ እንዲከበር ያዘጋጀወን የሻማ ማብራት ዝግጅት  ማርች 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ከ18.00 እስከ 19.30 መሃከለኛው የአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር ኮለን ከተማ ከሚገኘው የዶም ካቴድራል ፊት ለፊት ተግባራዊ አድርገናል፡፡ በጣም ሃይለኛ ነፋስ ስለነበር ሻማውን እያጠፋብን ችግር ቢፈጥርብንም፡ በጀርመንኛ የተዘጋጀውን ጽሁፍ በማደልና መፈክሮችን በማንጠልጠል ጀርመኖች እንዲያነቡና እንዲጠይቁ ማድረግ ተችሏል፡፡ በነፋሱ ሃያልነት ካሰብነው ሰዓት በፊት ለማቋረጥ ተገደናል፡፡

-ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታዎች ይፈቱ !!

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን